Schoolsfirst!

# ተማሪዎቻችን ይደግፉ፡ SPS Levies (የግብር ክፍያ) የካቲት 2025 ላይ ያድሱ



ተማሪዎቻችን እኛ ላይ የሚሞረኮዙ ናቸው። ትምህርት ቤቶቻቸው ከግዛት በሚቀርብላቸው እና በተማሪዎቹ ፍላጎቶች መካከል ያለውን የገንዘብ ድጋፍ ክፍተት ለመሙላት በመራጮች የጸደቀ የግብር ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ የግብር ገንዘብ ክፍያዎች አስፈላጊ ፕሮግራሞችን ይደግፋሉ፣ ሰራተኞችን ይደግፋሉ፣ ቴክኖሎጂን ለተማሪዎች በማቅረብ ለሁሉም ተማሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የመማሪያ አካባቢዎች እንዲኖሩ ያስችላሉ።

**እነዚህ የግብር ገንዘብ ክፍያዎች አዲስ ቀረጦች አይደሉም።** እነዚህ በቀላሉ አሁን ላይ ያለውን እና ግዜው እያለፈበት ያለውን የሴያትል የትምህርት ቤቶች የግብር ገንዘብ ድጋፍን የሚተኩ ይሆናሉ። እነዚህ እንዲታደሱ ማድረግ አስፈላጊ የሆነ የግንዘብ ድጋፍ በቦታው እንዲቆይ ያደርጋል። ከእነዚህ የግብር ገንዘብ ክፍያዎች ውጪ፣ ዲስትሪክቱ ይበልጥ የግንዝበ እጥረት ውስጥ ይወድቃል፣ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን ለመደገፍ አዳጋች ይሆንበታል።

## የግብር ክፍያ ማደስ አስፈላጊ የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው

**የትምህርታዊ ፕሮግራሞች እና አሰራሮች ግብር (Educational Programs & Operations Levy (EP&O)) እድሳት**

በግዛቶች በሚቀርበው የገንዘብ ድጋፍ እና SPS ሰራዎቹን ለማካሄድ በሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን መካከል የሚኖን ክፍተት ይሞላል

- **የተማሪ ደህንነት እና ድጋፍ:** የትምህርት ቤት ደህንነት፣ የልዩ ትምህርት እና የብዙ ቋንቋ ደጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ጨምሮ የሚከፈሉ ደመዎዞችን ይሸፍናል።
- **የተማሪ አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞች:** ልዩ ትምህርትን፣ ጤናማ የሆኑ የተማሪ ምግቦችን እና የተማሪ መጓጓዣን በቀጣይነት በገንዘብ ለመደገፍ ያስችላል
- **የተማሪ እድሎች:** ግዛቱ እንደ አትሌቲክስ፣ ስነ-ጥበብ፣ ሙዚቃ እና ድራማ ላሉ ከሰርዓተ ትምህርቱ ውጪ ለሆኑ እንቅሰቃሴዎች ምንም ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ አያቀርብም። ይህ ግብር ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍል ውጪ ለመማር እነዛን አስፈላጊ የሆኑ ዕድሎች እንዲያገኙ ያስችላል።

**የ Building Excellence VI (BEX VI) Capital Levy (የህንጻ ልህቀት የካፒታል ግብር)**

- የዘመኑን የመማሪያ እና የደህንነት መስፈርቶች የሚያሟሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ ዘመናዊ የትምህርት ቤት ሕንፃዎችን እንዲኖሩ ያስችላል
- እያንዳንዱ ተማሪ ለመማር ኮምፒውተር ወይም ታብሌት እንዲኖረው የሚያስችለውን ወሳኝ የቴክኖሎጂ የገንዘብ ድጋፍ ያቀርባል
- ትምህርት ቤቶቻችንን ጉልበት ቆጣቢ እንዲሆኑ እና ዝቅተኛ የስራ ማስኬጃ ወጪዎች እንዲኖሩ በማድረግ የታዳሽ ጉልበት ተነሳሽነትን ያበረታታል

## እንዴት መረዳት እንደሚችሉ፡

- **የገንዘብ ልገሳ ያድርጉ** የእርሶ አስተዋጽኦ በእነዚህ የግብር ገንዘብ ድጋፎች ላይ ይሁን የሚል ድምጽ ለማስጠት የሚያስችሉ የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ለመስራት ይራዳናል።
- **በበጎ ፍቃደኛነት ስራ ላይ ይሳተፉ:** መልእክቱን ለሌሎች በማዳረስ እና ትምህርት ቤቶቻችን እንዲጠነክሩ በማድረግ የጋራ ጥረት ላይ በበጎ ፈቃደኝነት ይሳተፉ።

**እያንዳንዷ ድምጽ ዋጋ አላት- ተማሪዎቻችንን በጋር እናግዝ!**

https://seattleschoolsfirst.org

መጀመሪያ በትምህርት ቤቶች የተከፈለ፣P.O. Box 2204, Seattle, WA 98111